

# ለጀግናዋ እየሩስ !

ከነቃጭሉ ወንድ = የሚባለው ተረት
ከንቱ ሆኖ ቀረ - የሌለው መሠረት ፡፡
ዘር ዘርታ ተኪታ - ጣይቱ አለፈች፣
ሴት ልጇቿን መርጣ - በአንድነት መረቀች ፡፡

አሉን በየዘመን የሚመጡ እንስቶች፣
የግፍ ቀንበር ሰብረው የሚታዩ ፈርጦች፡፡
አይተናል በቅርቡ ያስደመሙ ጦቢያን፣
ርዕዮት ዓለሙን ብርቱካን ሚደቅሳን ፡፡

የነሱን ጉድ ብለን አድንቀን ሳንጨርስ፣
የተስፋው ልጅ መጣች ጀግናዋ እየሩስ ፡፡
ታየች በሩቅ ጎልታ ጎፈር ጸጉሯን ደፍታ፣
የሴት አናብስቷ በጀግና ፈገግታ፣
የወያኔን አንጋች ሳትሰጥው ቦታ፣
በልበ ሙሉነት ፀንታ በእምነቷ፣
ጎምለል ብትልበት በጀግናው ደረቷ፣
ግቢውን አናጋው ተክለ ሰውነቷ ፡፡

ይህች ጀግና አናብስት እየሩሳሌም ተስፋው ግንቦት ሰባትን ለመቀላቀል በመንገድ ላይ እንዳለች ፣ በወያኔ እጅ ወደቀች ፡፡ ተይዛም ቅንጣት ታህል አልፈራችም ፡፡ በወያኔ ፍርድ ቤት ሳትከድ ፣ አዎ ! አምኜበት የትግል ሜዳውን ለመቀላቀል ስጓዝ ተይዣለሁ ፡፡ አሁንም እነግራችኋለሁ ! የአርበኞች ግንቦት ሰባት አባል ነኝ ፡፡ ከአላማዬ ንቅንቅ አታደርጉኝም ያለች ጀግና ናት ፡፡ ለዚህች ጀግና አናብስት ይህ ሲያንሳት ነው ፡፡